የሰ/መ.ቁ.74400

ግንቦት 7 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ግዮን ኢንዱስትሪያልና ኮሜርሺያል ኃ/የተ/የግል ማህበር-ነ/ፊጅ ያሬድ ወርቅዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ኃይሉ ናርዬ ጠበቃ ገ/እግዚአብሔር ኪዳኔ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የሚስተናገደውን የግል የስራ ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የመሰረቱት የስራ ግንኙነት ውል ከሕግ ውጪ የተቋረጠባቸው መሆኑን ገልፀው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ከተጠሪ ጋር የስራ ውል ግንኙነት ስለመኖሩ ሳይክድ የስራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪ ሲያሽከረክሩ በነበሩት በአመልካች ድርጅት ንብረት ላይ በግጭት ጉዳት ያደረሱ በመሆኑ ነው በማለት ስንብቱ ሕጋዊ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ በዚህ መልክ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ጉዳዩን በመመርመር ተጠሪ ጉዳት አድርሷል በማለት አመልካች የሚከራከረው የአመልካች ድርጅት እህት ኩባንያ የሆነው የግዮን ጋዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር ንብረት በሆነው ተሽከርካሪ ላይ መሆኑ መረጋገጡን፣ ተጠሪ የስራ ቅጥር ውል የፈፀሙት ከአመልካች ጋር እስከሆነ ድረስ የአመልካች ድርጅትና የግዮን ጋዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር ባለቤት አንድ መሆን ድርጅቶቹ የራሳቸው ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው እስከሆነ ድረስ በአመልካች ድርጅት ንብረት ላይ ተጠሪ ጉዳት አድርሰዋል ለማለት የማያስችል መሆኑን በምክንያትነት ይዞ የአመልካች እርምጃ ሕገወጥ ነው በማለት ደምድሞ ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎች ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ከእህት ኩባንያው ለስራ ተከራይቶ ሲጠቀም በነበረው ተሽከርካሪ ተጠሪ ጉዳት ያደረሱ ሁኖ እያለ ኩባንያዎቹ የተለያየ የሕግ ሰውነት ያላቸው ናቸው በማለት ስንብቱን ሕገወጥ ነው በማለት መወሰናቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪን የቀጠረውና ጉዳት የደረሰበት ተሽከርካሪ የአመልካች ድርጅት ሆኖ እያለ በአመልካች ድርጅት የደረሰ ጉዳት የለም ተብሎ ስንብቱ ሕገወጥ ነው የተለያዩ

ክፍያዎች ለተጠሪ ይፈጸሙ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ድርጅት የተጠሪ ቀጣሪ ፣ ተጠሪ ጉዳት አደረሰ የተባለበት ተሽከርካሪ ደግሞ የአመልካች ድርጅት ባለቤት የሆኑት ግለሰብ ባለቤት የሆኑበት ሁኖ ጉዳቱ ደረሰ በተባለበት ጊዜ አመልካች ድርጅት ተሽከርካሪውን ለራሱ ጥቅም በመገልገል ላይ በነበረበት ሁኔታ ተጠሪ ግጭት ያደረሱ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የህግ ሰውነት ያለው ሲሆን በዚህ ሕጋዊ ችሎታ የመከሰስም ሆነ የመክሰስ ችሎታ ይኖረዋል፡፡ አንድ የተፈጥሮ ሰው ከአንድ በላይ ኃ/የተወሰነ የግል ማህበሮች ባለቤት ሁኖ መገኘት በአንዱ ድርጅት ውስጥ ያለ ሰራተኛ በሌላኛው እህት ድርጅቱ ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉደት በሌላኛው ድርጅት ውስጥ በሕጉ አግባብ የተቀጠረውን ሰራተኛ በድርጅቱ ንብረት ላይ ጉዳት አድርሰሃል በማለት የስራ ውሉን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/ሸ/ መሠረት ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚስችለው ሕጋዊ ምክንያት አይደለም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/ሸ/ መሠረት የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ አሰሪው ሊያቋርጥ የሚችለው ሰራተኛው በአሰሪው ንብረት ወይም ከድርጅቱ ስራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው ማናቸውም ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ማድረሱ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ከያዛቸው ቁም ነገሮች ውስጥ "የአሰሪው ንብረት" እና "ከድርጅቱ ስራ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ባለው ማናቸውም ንብረት" የሚሉት ሐረጎች ይገኙበታል፡፡ ስለዚህ ጉዳት ደርሷል ለማለት መሟላት ካለባቸው ነገሮች አንዱ ንብረቱ የአሰሪው መሆኑና በቀጥታ ከድርጅቱ ስራ ጋር የሚገናኝ መሆኑ ነው፡፡ አሰሪ ማለት ደግሞ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 4 በተመለከተው መሠረት ቀጥሮ የሚያሰራ ግለሰብ ወይም ድርጅት ስለመሆኑ በተጠቃሹ አዋጅ አንቀፅ 2/1/ ስር ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ተፈጥሯል ሊባል የሚችለው የስራ ወሉ በአዋጁ አንቀጽ 4 መሠረት ሲመሰረት መሆኑንና በዚህ አግባብ የስራ ውሉ መመስረቱ ከተረጋገጠ የስራ ውል ግንኙነት በሕጉ አግባብ የሚገዛው ይህንኑ ውል በመሰረቱት ሰዎች መካከል ብቻ ይሆናል፡፡ የስራ ውል ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል የአዋጅ ቁጥር 377/1996 ተፈፃሚ የሚሆንበት ምክንያት የለም፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ተጠሪ ጋር የስራ ውል ግንኙነት መመስረቱ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች ተጠሪን ማሰናበቱን ሕጋዊ ነው በማለት የሚከራከረው የግዮን ጋዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር የሆነ መኪና ላይ በግጭት ምክንያት ጉዳት አድርሰዋል በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተጠሪ ከዚህ የተሽከርካሪው ባለቤት ከሆነው ድርጅት ጋር የፈፀሙት የቅጥር ውል የሌለ ሲሆን ተሽከርካሪውን አመልካች ለስራ ምክንያት ተከናትሮ ሲጠቀምበት የነበረ ወይም ንብረቱ ከድርጅቱ ስራ ጋር ቀጥታ ግንኙነት የነበረው ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ያልተረጋገጠ ነጥብ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ አመልካች ድርጅት ተጠሪ በሌላ ድርጅት ንብረት ላይ ጉዳት አድርሰዋል በማለት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የተመሰረተውን የስራ ግንኙነት ውል

ለማቋረጥ የሚስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የስራ ውሉን ከአመልካች ጋር መመስረታቸውንና ጉዳት ደርሶበታል የተባለው ተሽከርካሪም የአመልካች ድርጅት ባለቤት የሆኑት ግለሰብ የሆኑበት ግዮን ጋዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር መሆኑን በማረጋገጥ ስንብቱ ሕገወጥ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 2/1/ ፣ 4 እና 27/1/ሸ/ እና በንግድ ሕጉ ኃላፊነታቸው የተወሰነ የግል ማህበራት ስላላቸው ሕጋዊ ችሎታን በተመለከተ የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን ያገናዘበ ነው ከሚባል በስተቀር መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ፈጽመዋል ለማለት የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 55719 የካቲት 25 ቀን 2003 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 107754 ጥቅምት 16 ቀን 2004 ዓ.ም የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የአመልካች እርምጃ ሕገወጥ ነው ተብሎ ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

በዚህ ችሎት መጋቢት 05 ቀን 2004 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ዲ